
ኑብዮ ኑህ



ኣና
ዮጎርፋ ማዕበል

All right reserved

© የወጣቱ ተልዕኮ
የወጣቱ ተልዕኮ የኦንላይን እትም 2010
ሰሜን ወሎ ወልድያ

ahmedyesuf29@gmail.com
+251927790323
https://youth-mission.com



የወጣቱ ተልዕኮ

አህመድ የሱፍ

Presented by: Youth-Mission


Online Amharic Islamic

Books Publishing.


بسم الله الرحمن الرحيم

ከረዥም ጊዜ በፊት ወድ ፣ ሱዋእ ፣ የጉስ ፣ የኡቅ እና ነስር (የሚባለ) ተብለው የሚጠሩ አምስት መልካም ሰዎች ነበሩ።

እነዚህ ሰዎች በሞቱ ጊዜ ለእነሱ ማስታወሻ የሚሆን ሃውልት እንዲያቆሙላቸው አነሳሳቸው።




ቀስበቀስ ሰዎቹ እነዚህን ሃውልቶች ጣኦቶቻቸው አድርገው ያዙ። አሏህን ብቻ ስለ ማምለክ (ስለ መገዛት) ረሱ።

አሏህ ነብዩ ኑህ (ዐ.ሰ) የላካቸው ሰዎችን ወደ ተውሂድ ፣ አሏህን ብቻ እንዲገዙ እና ከሽርክ የውሸት አማልክትን መገዛት እንዲከለከሉ ነው።

ኑህ (ዐ.ሰ) ህዝቦቻቸውን ለ950 አመታት አስተምረዋል። ነገርግን ብዙዎቹ ሳይቀበልቸው ቀሩ አልተቀበሏቸውም። አላመኑም።






ከዚህ የበለጠ ህዝቦቹ እንደማያምኑ አሏህ ለኑህ (ዐ.ሰ) ነገራቸው። እናም ኑህ (ዐ.ሰ) ትልቅ መርከብ እንዲሰሩ አሏህ አዘዛቸው።

አሏህ የኑህን ህዝቦች በጎርፍ ሊቀጣቸው ፤ ከኑህ ጋር በመርከቧ ውስጥ ያሉ አማኞችን ሊያድናቸው ነው።

ዘወትር ከሃዲዎች በኑህ ጎን ሲያልፉ ያላግጡባቸዋል፤ ስይስቁባቸዋል። ነገርግን ኑህ (ዐ.ሰ) በአሏህ ቃልኪዳን እምነት ስለላቸው ‹‹አሁን በእኛ ላይ ትስቃላችሁ ግን በቅርቡ በእናነተ ላይ እንስቃለን።›› ሲሉ ለከሃዲያኖች መለሱላቸው።






በመጨረሻ አንድ ቀን ከኑህ ምድጃ ውሃ ፈለቀ፤ ያ አሏህ ከሃዲያኖችን ለመቅጣት ጎርፍ ሊልክ መሆኑን የአሏህ ምልክት ነበር።

ዝናብ ከሰማይ በሃይል ዘነበ፤ ምድር በውስጧ ያለውን ውሃ ወደ ላይ ተፋች።


ኑህ (ዐ.ሰ) ከቤተሰቦቻቸው ፣ ከአማኞች ጋር እና ከየእንስሳ አይነቱ ሁለት ሁለት ሴትና ወንድ አድርገው ወደ መርከቧ እንዲወስዱ አሏህ አዘዛቸው።።

የኑህ ሚስት እና ልጃቸው የምበመርከብ ላይ አልተሳፈሩም ነበር። ከሃዲዎች የነበሩ መሆኑን አሏህ ለኑህ ነገራቸው።።



ውሃው እየጨመረ እየሞላ መጣ። ኑህ ልጃቸውን እኔ ጋር ና ሲለ ጠሩት። ልጃቸው ጥሪያቸውን ሳይቀበል ቀረ።ከጎርፉ ለማምለጥ ወደ ተራራው ጫፍ እሄዳለሁ ሲል መለሰላቸው። ኑህ ዛሬ ከአኗህ ቅጣት ማምለጫ መንገድ ምንም የለምና ሲለ በድጋሜ ጠሩት።

ማዕበለ በመካከላቸው መጣ። የኑህ ልጅ ከከሃዲዎች ጋር ሰምጦ ሞተ።




አማኞቹ አሏህ ከከሃዲዎች ስላዳናቸው አሏህን አመሰገኑ። ደህንነቱ የተጠበቀና የተባረከ ቦታ እንዲያሳርፋቸው አሏህን ለመኑ።



ምድር ሙሉ በሙሉ በውሃ ተሞልታለች ፣ ከሃዲዎች ጠፍተዋል።እናም ሰማይ ማዝነቧን እንድታቆም ፣ ምድር የተፋችውን ውሃ እንድትውጥ አሏህ አዘዛቸው።

ውሃው ሲጎድል መርከቡ ጁዲ ተራራ ላይ አረፈ።።



ኑህ እና አማኞቹ ከመርከቡ በሰላም እንዲወርዱ አሏህ ነገራቸው።። አሏህ ባረካቸውም።። የኑህ (ዐ.ሰ) ሶስት ወንድ ልጆች፡ ሸም ፣ ሐም ፣ ጃፍ ናቸው።።

ቀሪው የሰው ልጅ አንዴ በድጋሚ ተወለዱ፤ በምድር ላይ መኖር ጀመሩ።።


رَبَّنَا تَقَبَّلْ مِنَّا إِنَّكَ
أَنْتَ السَّمِيعُ العَلِيمُ

ማንኛውም አይነት ሃሳብ አስተያየት ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወልልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.com ይጎብኙና መልዕክት ያስቀምጡልን። ጀዛኩሙሉህ ኸይረን ከሲረን!